# ኑሮ ያለ ነጻነት ግማሽ ሞት

የሰዉ ልጅ መሰረታዊ ፍላጎቶቹ "ሶስት" ናቸዉ ይባላል። ልብስ፣ መጠለያ እና ምግብ መሆናቸዉ ነው። እውነቱን ለመናገር ሶስት ብቻ አይመስሉኝም። የሆነ ሆኖ ዋናው እና መሠረታዊ ፍላጎታችን ግን ሜዳ ላይ ወድ ቋል። እነዚህ "ሶስት" ተብለው በሰፊው የሚነገሩት ፍላጎቶች የሰው ልጅ ፍላጎቶች ብቻ ሳይሆኑ የእንስሳትም ናቸው። ላሞች ፤ በሬዎች ወዘተ እነዚህን ነገሮች ይፈልጋሉ ። በመሆኑም እነዚህ መሰረታዊ ፍላጎቶቹ የህያዋን ሁሉ መሰረታዊ ፍላጎቶቹ ቢባሉ ትንሽ ስሜት ይሰጣል።

የሰዉ ልጅ መሰረታዊ ፍላጎቶቹ "ሶስት" ብቻ አይደሉም አራት ናቸው ። አንዱና ዋንኛው ፍላጎት ነጻነት ተብሎ ይጠራል። እነዚህን "ሶስት" ፍላጎቶች ሁሉ የሚገዛዉና የሚያስተዳድረው ይህ የሰዉ ልጆች ፈቃድ ነዉ። የፈለገዉን መልበስ ፤ የፈለገዉን መብላት፤ በፈቃዱ መውጣት እና መግባትን ከተነፈገ እነዚ "ሶስት" ፍላጎቶቻችን ህልው አይኖራቸውም።

ነጻነት የፈቃዳችን ተግባራዊ መገለጫው ነው። እኛ የሰው ልጆች ከሌሎች እንስሳት የለየን ትልቁ ነገር የራሳችን የጠራ ህሊና ፈቃድ /will/ ያለን ፍጡራን ሆነን መገኘታችን ነው;; ፈቃዳችን ውጪያዊ ልምምዶችና አካባቢዎች ተጽዕኖ ይፍጠሩበት እንጂ ከመሰረቱ ግን የስሪታችን አንዱ አለባ ነው። ስጋ ና ደም ብቻ ሳንሆን የጠራ ፈቃድ ያለን ክቡር ፍጡራን ነን።

በርግጥ ነጻነት አንጻራዊነት አለው። የእኛ የሰው ልጆች የህይወት ጥራትም በየለቱ በምንሰፍረው የነጻነት ልክ ሊለካ ይችላል። ነጻነት የመኖር /survival/ ጥያቄ በመሆኑም ነው ከመሰረታዊ ፍላጎቶች ሊመደብ ይገባዋል የሚያሰኘን።

እስቲ በምናብ ሆነን የሰው ልጅን ያለ ነጻ ፈቃዱ ራቁቱን እንየው ። ግላዊም ይሁን ማህበራዊ ፈቃዱ የታፈነበት ሰው ምን ይመስላል? ስለፍጹሙ ነጻነታችን ወይም ፈቃዳችን ስናወራ የሰው ልጅ ሙሉውን ነጻነት ሲያጣ ሙሉዉን ሞት ሞቷል ማለት ነዉ። አይበላም፤ አይጠጣም፤ አይለብስም በአንድ ቃልም ፈቃድ የለዉም። ታዲያ ከዚህ በመለስም ሌላ ሞትም አለ;; እየበላና እየጠጣ ግማሽ ሞትን ሞቶ ወይም በሩብ ህይወት እየኖረ ላይኖር ይችላል። አሳዛኙ ህይወትም ይሄዉ ነዉ። በስነ-ቃሉም "ኑሮ ካሉት መቃብር ይሞቃል" እያለ ግማሹን መሞቱን አምኖ የግማሽ ህይወት ከመኖር ሙሉዉን ሞቶ መገላገሉ ሳይሻል አይቀርም አይነት ነፍሱ ትሰብቃለች።

ስለ ሙሉዉ ነጻነታችን ስናወራ ይህ ሙሉዉ ፈቃዳችን ልጓም የለውም ማለት አይደለም። ቤታችንን ዘጋግተን ከጓዳ ሳሎን ራቁታችንን ወዲያ ወዲህ መንጎራደድ እንችላለን። ይሁን እና ቢያሰኘንም እንኳ በአዉራ ጎዳና ወጥተን ራቁታችንን አንንዘላዘልም። ምክንያቱም ይህ በማህበራዊዉ ስምምነታችን መሰረት ህቡዕ/ taboo ነዉ ስላልን ለጊዜዉ ይህን የዳዳንን ፈቃድ በማህበራዊዉ ስምምነታችን ማጣቀሻነት በገዛ ፈቃዳችን እንሸረዋለን;; ድምጽን በድምጽ እንሽራለን ማለት ነዉ። ታዲያ ይህን ፈቃዳችንን በመከልከላችን ጸጸት አይሰማንም። ፈቃዳችን ከፈቃዳችን መክሮበታልና ። ህይወታችን

ሁሉ በምርጫ የተሞላ ነዉ። ስንራመድ መርጠን ፤ ስንበላ መርጠን ፤ ስንናገር መርጠን ፤ ስንለብስ መርጠን ፤ ስንጽፍ መርጠን ፤ ስንጋባ መርጠን ተማርጠን ፤ ስንሰማ መርጠን ፤ ብቻ ሁሉን መርጠን ነዉ። በዚህ የህይወት ጎዳናችን ባሉ ምርጫዎች ሁሉ የበላይ የሆነዉ ፈቃዳችን ነዉ። ፈቃዳችን ፍላጎቱን ከማህበራዊዉ ስምምነት ጋር እያገናዘበ ህይወታችንን ይመራል። ምርጫችን ወይም ፍቃዳችን እጁ ሲጠመዘዝ እና ያልፈለግነዉን እየመረጥን እንድንኖር ስንገደድ ግማሹን ሞተን ጨርሰን በግማሹ እንኖራለን ሲከፋም በሲሶ ህይወት ኑሮ ካሉት መቃብር ይሞቃልን እያዜምን ስጋን እንገፋለን ማለት ነዉ።

ቆይ ግዴለም ጠበብ አርገን እንወያይ ። ለመሆኑ በነጻዉ ፍቃዳችን ግዛት ላይ የሚገቡ ባእድ ተጽዕኖዎች ምንጮቻቸዉ ምን ምን ናቸዉ? የሚለዉን ጠቃሚ እና ተግባራዊ ጉዳይ አንስተን ምናባችን በከፈተዉ ልክ እንወያይ ።

## የነጻዉ ፈቃዳችን ጭነቶች

1. እኛዉ ራሳችን ።

በነጻነታችን ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ከሚያሳድሩ ጉዳዮች መካከል አንዱ እኛዉ ራሳችን ን ከመጨቆናችን ይጀምራል ። ነጻ ፍጡር መሆናችንን ከልብ አምኖ መቀበል የሌሎች ግለሰቦችን ፈቃድ ማመን እና ማክበር የነጻነታችን መሠረት ነው። ራሳችንን በራሳችን መጨቆን ወይም ለጭቆና ማመቻቸት ተገቢ አይደለም። ይህ በተፈጥሮአዊ ነጻነታችን እና በራሳችን ጭቆና መሃል የሚፈጠ ረው ግጭት ደባል ስብዕና እንድናዳብር ያደረጋል።

ሌላው ስለ ግለሰብ ነጻነት ስናወራ ተክለ ሰውነትን ማረቅ እና ማስተካከልንም ይጨምራል ። ነጻነት የትምህርት አውድም ነው ። ራስን ማስተካከል መሞረድ ከዚያም ለማህበራዊ ኑሮ ብቁ አድርጎ ማቅረብ ይጠበቃል። በነጻነታቸው ያመኑ ፤ የሌላውን ነጻነት ያከበሩ የሚበዙበት ማ/ሰብ ጤነኛ እና ለጨቋኞች የማይመች ህብረተሰብ ይወጣዋል። በአንጻሩ እራሳችንን እየጨቆንን ለሰው ልጅ የሚገባዉን ክብር ለራሳችን ነፍገነው የምንኖር ከሆነ የእንደዚህ አይነት ዜጎች ድምር ውጤት የሚፈጥረዉ ማ/ሰብ ጤነኛ አይሆንም። በርግጥም ይህ ራስን የመጨቆኑ ጉዳይ ከአካባቢ ተፅዕኖ ሊመጣ መቻሉን እንገነዘባለን። ይሁን እንጂ በተፈጥሮ ያለውን ፈቃዳችንን በዉስጣችን መንከባከብ ከውጪያዊ ተፅዕኖዎች መጠበቅ ጠቃሚ ነው። ቡድን የግለሰቦች ውጤት ነው;;ግለሰቦች ቡድንን ሲሰሩ ቡድን ግን ግለሰቦችን አይሰራም;;በመሆኑም የግለሰቦች ነጻነት የቡድንን ህይዎት ጥራት በብዙ ይወስነዋል;;ራሳችንን ነጻ አድርገን ካልተነሳን ነጻነታችንን የገፈፈውን የተደራጀ ቡድን ሰፊ እድል እንሰጠዋለን ;;በብዙ እጅ ነጻነታችንን የዘረፈውን ለመታገል የ እያንዳንዳችን ስብእና ሁኔታ ትግላችንን ይወስነዋል;;

በተደጋጋሚ ከሚደርስብን ጭቆና የተነሳ ፤ ማስመሰል ፤ ውሸት ፤ ፍርሀት ፤ ስጋት ፤ርስ በርስ ያለመተማመን; የመሳሰሉትን የስነ ልቦና ቀውሶች ሊያመጣብን እንደሚችል ማወቅ ይህም ነፃነታችንን እንደሚጫነው ማሰብ ይጠቅማል ። ውሸትን የሚናገር ነፃነት የለውም። ኢትዮጵያ በግብሯ ያቋቋመችው

ቴሌቪዥን እና ሬድዮ እንኳን ከሰአት ውጪ እውነትን አይናገርም እስከመባል ደርሷል ። እንግዲህ በዚያ የሚሰሩ ጋዜጠኞች እየዋሹ ነፃነት አላቸው ማለት አይቻልም። ይህን የስነ ልቦና ቀውስ እያዳበሩ ይመጡና ቀስ እያሉ ከሰውነት ተራ ይዎጡና ስጋና ደም ብቻ ይሆናሉ ። እንግዲ ስለ ነፃነት ካወጋን እነሆ የመጀመሪያው የነፃነት ደረጃ ወይም ቅንጣት ያለው በገዛ እጃችን ነው። ሌላው በነፃነት የማመናችን ተግባራዊዉ ገፅታ ደግሞ ሌላ ባእድ አካል ነፃነታችንን ወይም ፈቃዳችንን ሊጫን ሲመጣ እምቢኝ ብሎ መታገል ነው።

## 2. <u>***ወግ ልማዶቻችን***</u>

እኛ ኢትዮጵያውያን በጣም የሚያኮሩን ፤ የሚያስደስቱን ፤ ሰብአዊነትን የሚያዳብሩ ፤ ነፃነትን የሚያዳብሩ ወግና ልማዶች ብዙ አሉን። ይሁን እንጂ አንዳንድ የግል ፈቃዳችንን የሚጫኑ ነፃነትን የሚፃረሩም እንዳሉን እንመን። ኢትዮጵያችን ግለሰቦች የፈለጉትን እምነት ተከትለው የሚኖሩባት ፤ የፈለገዉን በልቶና ጠጥቶ የሚታደርባት ፤ የፈለገውን ለብሶ የሚታዩባት ልትሆን ይገባል። በእምነት በኩል ሲታይ በክርስቲያን ኢትዮጵያውያን እና በሙስሊም ኢትዮጵያውያን በኩል የሚታየዉ መግባባት በፕሮቴስታንቱና በኦርቶዶክሱም ሊገለፅ ይገባዋል ። ስለ ነፃነት ስናወራ አንዱ የነፃነት ፍላጎት ከዚህች ዓለም ባሻገር ግለሰቦች ያላቸውን ተስፋ ማክበር ነው።

በተለያዩ ባህል ክንዋኔዎች ወቅት መግባባት፤ መረዳዳት ተገቢ ነው። በአመጋገብ ጊዜ ለጤናዬ ይጠቅመኛል ያለውን ሲመገብ ከማህ/ሰብ ማግለል እና ነፃነቱን መግፈፍ የለብንም ። ግለሰብ ያለውን ለብሶ ይታይ ። የፈለገውን በመልበሱ አናሸማቀው ።ከፀጉር አሰራሯ እስከ ጥፍሯ ያሻትን ትሁን። አናሸማቃት። ተወልጄ ባደኩበት ከተማ ሴት ልጅ በለበሰችው ትሸማቀቅ ነበር። እነዚህን እና እነዚህን የመሳሰሉ ልማዶች መተው ይጠበቅብናል ። ሙሉውን ነፃነታችንን ከልባችን ከሻትን አንዱ ነፃነታችንን የተጫነው በጉያችን ያሳደግነው ወግ ልማድም ነዉ። ይህንን ርግፍ አርጎ ለመተው ብዙ ብር መጀመሪያ ማግኘት ያለብን አይመስለኝም ። ብር ማግኘት ከእንዲህ አይነቱ ሥነ ልቦና ለመላቀቅ ዋስትናም አይመስለኝም ።

3. **የመንግስት ጭቆና**

በመሰረቱ ለፅሁፌ መነሻ የሆነኝ ይሄው ነበር ። እንዴው ስለዚሁ ሳውጠነጥን ነው እነዚያ ወደ ልቤ የመጡት;; ይህ አይነት ጭቆና በአንድም በሌላም መልኩ ከላይ ለጠቀስናቸው ሁለት የጭቆና አይነቶች ሰፊ አስተዋፅኦ ያለው ነው ። ከፍ ሲል ያነሳናቸው የጭቆና መስመሮች ለዚህ ለዋናው ጨቋኝ ገባሮች ናቸው;; መንግስት በተደራጀ ሁኔታ ሲጨቁን መላው የህይወት አቅጣጫዎቻችንን ይነካል። ይህ ጭቆና በአይነቱም ሆነ በይዘቱ ግዙፍ በመሆኑ ነዉ የከፋ ጭቆና የሚያሰኘን ።

ዓለም እየተሻሻለች ባለችበት በአሁኑ ወቅት በአገራችን ኢትዮጵያ ግን ጭቆና ጥበባዊነትን እየያዘ ፤ እየረቀቀና እያደገ መጥቷል።

ስለ ፈቃዶቻችን ስናወጋ መብቶቻችንን እንቁጠር;; እጅግ ብዙው ብዙ ሃይል በታጠቀ ቡድን ታስሮብን እናያለን ። እኛ ኢትዮጵያውያን ያላመንበትን እንሰራለን ፤ ያልፈቀድንለት ይገዛናል ፤ የተሰማንን አንፅፍም የልባችንን ለመጻፍ መዘለል አለብን። ሰብአዊ መብቶቻችን ያለልክ ከስተዋል ፤ ተማሪው አካዳሚክ ነፃነት የለውም ፤ ምሁሩ በነፃነት አይመራመርም ፤ አያስተምርም ። ነጋዴው ነፃ ገበያ ይናፍቃል ፤ ገበሬው ተፈጥሮ የሰጠችውን መሬቱን ለተደራጀ ቡድን አስረክቦ እየገበረ ይኖራል ፤ ባለሙያዎች ለሙያቸው የገቡትን መሃላ እንዲሰብሩ ይገደዳሉ ፤ ገዥው ሲፈልገው ፅፎ ሲፈልገው ባልተፃፈ ህግ ዜጎችን ያስራል ፤ ይገድላል ። የፈለግነውን የፖለቲካ መስመር መከተል እስከ ዘር ማጥፋት በሚደርስ ያስወነጅላል;; ክቡር ዶክተር ብርሃኑ ነጋ እንዳለው እውነትን መግለጥ ወንጀል ነው ዛሬ ባገራችን። አማራጭ ሃሳብ ይዞ መምጣት በስነ ልቦናና በአካል የሚያስቀጣ ሆኖ ወደ ጠቅል ያረጀ አስተዳደር እያደግን ነው። ግፍና በደልን አድልዎን ሁሉ ተሸክመን ደሞ ኑሮ ብለነው እንኖራለን;; ይህን ሁሉ ግፍ ተሸክመን የምንኖር ሰዎች ዲሞክራሲ ይከብዳችሁዋል ተብለን በነዚሁ በገዢዎች ተፈርዶብናል። የነሱን ግፍ እና አመጽ የተሸከመው ሰፊው ትከሻችን የተፈጥሮ ፍላጎታችንን ነጻነትዬን እንዴት መሸከም እንደሚያቅተን እነሱና ዲያቢሎስ ብቻ ናቸው የሚያውቁት;; ዴሞክራሲ ሸክሙ ለዚብ ቀንበሩም ቀሊል ነው። አንዳንዴም ትምህርት

ያንሳችሁዋልም ይባላል;;አገር እየበጠበጠ ያለው ያልተማረው ገበሬ ይመስል;;ለ ዴሞክራሲ ምንም አይነት ቅድመ ሁኔታ አያስፈልግም;; የሚያስፈልገው አንድ ነው እሱም ሰው ሆኖ መፈጠር ብቻ ነው;;

ስለ ነፃነት ስናወራ አንዱና ትልቁ ነገር ፈቃዳችን /Will / መከበሩ ነው። ያልፈቀድንለት ሲመራን፤ ያለፈቃዳችን ስንወጣና ስንገባ በርግጥም ግማሹን ሞት ጨርሰን በግማሹ እየኖርን ነው ማለት ነው ። ይህ ግማሽና ሩብ ህይወት እጅጉን መራራ ነው ። ከተፈጥሮ ፈቃዳችን ስለተገነጠልን ያንን ቅድም ያልነዉን ዜማ እንዘምራለን ። “ኑሮ ካሉት መቃብር ይሞቃል” ።

የኢትዮጵያ መንግስት በአንድ ገጽታው ወታደራዊ በሌላው መልኩ ደሞ የጦፈ ነጋዴ ነው። ከትንሽ እስከ ትልቅ የንግድ ተቋማትን ከፍቶ ይሸጣል ይለውጣል ። ተራው ነጋዴ በተረፈችው ነፃነት የሚመላለስ ሲሆን ብዙውን ነፃነቱን ለመጣል የቀረጠው ትንሽ በር ተከፍቶለት ጥቂት ብር ይሰራ ይሆናል ። ፍትህ አልባ የንግድ ስርኣት የመታት አገር የኑሮ ውድነት እና የድህነት እድገት ያነግባት ይዟል;;

- **እንደ መቋጫ**

ትዝ ይለኛል አንድ አስተማሪ ጓደኛዬ ከአመታት በፊት ያጫወተኝ ። አንድ የህ/ሰብ ሳይንስ መምህር ለተማሪዎች የመጀመሪያ ሴሚስተር ፈተና የሚሆን ጥያቄ ያዘጋጃል ። ያዘጋጀው ጥያቄ ከመፅሃፍ በተዘዋዋሪ ይሁን በቀጥታ የተቀዳ ነው። ጥያቄው እንዲህ ነበር ;;

በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ ከሚከተሉት መሪዎች መካከል ዴሞክራት መሪ የትኛው ነው?

ሀ፡ አፄ ሀይለስላሴ

ለ: ኮሎኔል መንግስቱ ሀይለማርያም

ሐ: አቶ መለስ ዜናዊ

መ: ሁሉም;; የሚል ነበር።

የሚገርመዉ አንዱ ተማሪ "ሠ" ብሎ ሌላ ምርጫ ከራሱ ሰጥቶ ያንኑ ደግሞ ከቦ መገኘቱ ነበር ። ይህ ወጣት የሠራው አዲሱ ምርጫ "ሠ" መልስ የለም;; የሚል ነበር ። ነፃነቱን የሰራ ብልህ ተማሪ ነው ። ነጻነታችንን መከበብ ይጠበቅብናል;;መንግስት ምርጫ ሲያሳጣን ምርጫ መፍጠር ነው;;ፈቃዳችንን ካልመረጥን እና ቅጥር ካልሰራን የሌላውን ፈቃድ የማያከብሩ የህይዎት ፍልስፍናቸው ሆድ ብቻ የሆኑ ሰዎች ወደ ፈቃዳችን ይገቡና ያልፈቀድነውን እያረግን እንዞ ከነጻነት ጎድለን እንኖራለን;;

እጅጉን የከፉ ጭቆና ውስጥ የምንገኝ እኛ ኢትዮጵያዊያን የጣልነውን የአባቶች ወኔ ማንሳት አለብን ። ታሪካችንን ወደኋላ ስናይ አባቶቻችን በዚያን ጊዜ አለም ለነጻነት ከሰጠችው ዋጋ በላይ ከፍ ያለ መረዳት ረግጠው እንደነበር ምስክሩ በቅኝ ግዛት ያለመገዛታችን ነው ።እየኖርን ከምንሞት ሞተን ብንኖር አይሻልም ?

አስተያየት ያሳድጋል!

geletawzeleke@gmail.com